ROCKVILLE, MARYLAND

# 2ኛ የውጤት መስጫ ክፍለጊዜ የ 1ኛ ክፍል የወላጆች መመሪያ

በማርክ መስጫ 2 ወቅት፣ የ1ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለጸው ፅንሰሀሳቦችና ክህሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።

እባክዎ ልብ ይበሉ፡- በ በኢታሊክስ የታዩት ጽንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ትምህርት ተሰጥቶባቸዋል ነገር ግን በሪፖርት ካርዱ ላይ ደረጃ/ዉጤት አልተገለጸም።

## ሒሳብ

### ቁጥሮችና ግብረቶች በአስሮሽ ቤት

- የባለ-ሁለት-አሃዝ ቁጥር ሁለቱ አሃዞች የአስሮሽ እና የአህዱዎች መጠኖች እንደሚወክሉ መገንዘብ።

### ስሌቶች እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን በቅልጥፍና መደመር እና መቀነስ።
- በ20 ቁጥር መካከል ያሉ አሃዞችን የሚከተሉትን ስልቶች በመጠቀም መደመር እና መቀነስ—
    - o በመቁጠር፤
    - o በዚህ መልክ አስር በማድረግ(ምሳሌ፣ 8 + 6 = 8+2+4 = 10+4=14)፤
    - o ወደ አስር የሚመራ ቁጥርን መበተን (ለምሳሌ፡- 13-4=13-3-1=10-1=9)፤
    - o በመደመር እና በመቀነስ መካከል ባለው ግንኙነት በመጠቀም (ለምሳሌ፣ 8+4= 12 እንደሚሆን በማወቅ፣ 12-8= 4) እንደሚሆንም ይታወቃል፤ እና
    - o ተመጣጣኝ ነገር ግን ቀላል ወይም የሚታወቅ ድምር መፍጠር (ለምሳሌ፡- 6 + 7 በመደመር የሚታወቀውን ተመጣጣኝ መፍጠር 6+6+1=12+1=13)።
- በሁሉም ቦታዎች ያልታወቁ ያሉበት በ20 ውስጥ መደመርና መቀነስን በመጠቀም የማከል፣ የመቀነስ፣ ኣንድላይ ማሰባሰብ፣ መበተን፣ እና የማወዳደር ሁኔታዎችን የሚያካትቱ የቃል ፕሮብሌሞችን መፍታት።
- ድምራቸዉ (ጠቅላላ) ከ20 የሚያንስ ወይም እኩል የሆነ ሶስት ሙሉ ቁጥሮችን የሚያካትቱ የቃል ፕሮብሌሞች መፍታት።
    - o ፕሮብሌሙን ለመወከል በነገሮች፣ ስእሎች፣ እና ቀመሮች ከምስል ጋር ላልታወቀው ቁጥር መጠቀም።
- መቁጠርን ከመደመር እና መቀነስ ጋር ማዛመድ (ለምሳሌ፣ 2 ለመጨመር 2 ላይ መቁጠር)።
- የእኩል ምልክትን ትርጉም መገንዘብ፣ እናም መደመርና መቀነስ የሚያካትቱ ቀመሮች ትክክል ወይም ስህተት መሆናቸውን መወሰን።

## ምንባብ

### መሰረታዊ ክሂሎቶች

- ስለ ማተም አደረጃጀት እና መሠረታዊ ባህርይ ግንዛቤ መግለጽ/ማስረዳት።
- የንግግር ቃሎች፣ ፊደላት/ክፍለ ቃላት፣ እና ድምፆችን (ስነ ልሳን) መረዳት/መግለጽ።
- ቃላትን በመነጣጠል/በመለየት ለክፍል ደረጃ የሚመጥን ስነ-ቃል እና የቃላት ትንታኔ ክህሎት ማወቅ እና መተግበር።
- በአእምሮ የመያዝ ችሎታ/መረዳትን ለማገዝ በትክክል በብቃት እና በማቀላጠፍ ማንበብ።

### የማንበብ ግንዛቤ፡- ስነ ፅሁፍ

- ከጽሑፍ ውስጥ ስለ ቁልፍ ዝርዝሮች ጥያቄዎችን ይጠይቁ እና ይመልሱ።
- ታሪኮችን እንደገና መንገር፣ ዝርዝሮችን ጨምሮ፣ እናም የማእከላዊ መልእክታቸውን ወይም ትምህርታቸውን ግንዛቤ ማሳየት።
- ከታሪክ ውስጥ ገጸ-ባሕርይ፣ ዝግጅትን /መቼት እና ዋና ክዉነቶችን፣ ቁልፍ ዝርዝሮች እና ሥዕላዊ መግለጫ በመጠቀም ማብራራት።
- በታሪኮች ውስጥ የገፀባህርያትን ጀብዱዎችና ተሞክሮዎች ማወዳደርና ማነፃፀር።
- ከቅስቀሳና ድጋፍ ጋር፣ ለ1ኛ ክፍል ተገቢ ውስብስብነት ያለው ስድ ንባብና ግጥም ማንበብ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፡- መረጃዊ

- የኣንድን ፅሁፍ ዋናውን ርእስ መለየት እና ቁልፍ ዝርዝሮችን መልሶ መንገር።
- በጽሑፉ ውስጥ የቃላትን እና ሀረጎችን ትርጉም ለመወሰን ወይም ለማብራራት እንዲረዱ ጥያቄዎችን ይጠይቁ እና ይመልሱ።
- ቁልፍ ሃሳቦቹን ለመግለፅ በፅሁፍ ውስጥ በሚገኙ ስእሎችና ዝርዝሮች መጠቀም።
- ከቅስቀሳና ከድጋፍ ጋር፣ ለ1ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆነ መረጃያዊ ፅሁፍ ማንበብ።

### ቋንቋ፡- የቃላት እውቀት እና አጠቃቀም

- ዘለግ ባለ/በጎላ ድምፅ ከተነበበ ጽሑፍ ላይ ወይም በቃላት ወይም በሌላ ሚዲያ የቀረቡ መረጃዎችን በተመለከተ ቁልፍ ዝርዝሮችን ይጠይቁ እና ይመልሱ።
- በ1ኛ ክፍል ምንባብና ኣውደንባብ በመመስረት፣ ከድርድር ስልቶች በተለዋዋጭነት በመምረጥ፣ ያልታወቁና ባለ-በርካታ-ትርጉም ቃላትና ሃረጎች ትርጉም መወሰን ወይም ማብራራት።
- ያልታወቁ ቃላት ትርጉም ለመወሰን የዓረፍተ ነገር አውድን መጠቀም።
- ኣዘውትረው በሚታይ ተለጣፊዎችንና የስር ቃላትን ለቃላት ትርጉም እንደ ፍንጭ ኣድርጎ መጠቀም።

## ጽሑፍ

### መረጃ የሚሰጥ/ትምህርታዊ/ገላጭ

- በአነስተኛ ቡድን ለውይይት አንድ ርእስ ላይ ጥያቄ ማንሳት።
- እነርሱ በሚያነሱት ርእስ ላይ ትምህርታዊ/የማብራሪያ ጽሑፍ መጻፍ እና ስለ ርእሱ አንዳንድ ማስረጃ/እውነታ መስጠት እና መደምደሚያ ሃሳብ መስጠት።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- በጋራ የሚካሄድ ጥናት ላይ መሳተፍ።
- በኣንድ ርእስ ማተኮር፣ ከእኩያዎች ለሚመጡ ጥያቄዎችና ምክሮች ምላሽ መስጠት፣ እና እንዳስፈላጊነቱ ፅሁፍን ለማጠናከር ዝርዝሮች መጨመር።
- ጽሑፍ ለማዘጋጀት እና ለማሳተም የተለያዩ ዲጅታል መገልገያዎችን መጠቀም፣ ከእኩያሞቹ ጋር መተባበርን ጨምሮ።
- ከልምድ/ገጠመኝ የተገኘ መረጃ በማስታወስ/በመጥቀስ ወይም ከተሰጡ ምንጮች መረጃ በመሰብሰብ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት።

### የቋንቋ አጠቃቀም

- ሰዎችን፣ ቦታዎችን፣ ግዑዝ እቃዎች፣ እና የተፈጸሙ ድርጊቶችን በዝርዝር አግባብ የሆኑ ሃሳቦችን እና ስሜትን በመግለጽ ማስረዳት።
- ስዕል ወይም ሌላ የሚታዩ ነገሮችን አስፈላጊ ከሆነ በመጨመር አመለካከቶችን፣ አስተሳሰቦችን፣ እና ስሜቶችን ማብራራት/መግለጽ።
- ለስራ እና ለትክክለኛ ሁኔታ አግባብነት ሲኖራቸዉ የተሟሉ ዐረፍተ ነገሮችን ማፍለቅ።
- በመፃፍ ወይም በንግግር የመደበኛ እንግሊዘኛ ሰዋሰውና ኣጠቃቀም ደንቦች በቂ ችሎታ ማሳየት።
- በግል፣ በይዞታ/ንብረትነት፣ እና ባልተወሰኑ ተውላጠስሞች (ለምሳሌ፣ I, me, my; they, them, their, anyone, everything) መጠቀም።
- ያለፈውን፣ የኣሁኑን፣ እና የወደፊቱን መንፈስ (ለምሳሌ፣ Yesterday/ትናንት ወደቤት ሄድኩኝ/walked፤ Today/ዛሬ ወደ ቤት እሄዳለሁ/walk፤ Tomorrow/ነገ ወደ ቤት እሄዳለሁ/will walk) ለማስተላለፍ ግሶችን መጠቀም።
- ዘወትር የሚደርሱ ቅፅሎችን፣ መስተፃምሮችን፣ እና ወሳኞችን ኣገልግሎት ላይ ማዋል።
- በፅሁፍ የመደበኛ እንግሊዝኛ በትልቅ ፊደል ኣጠቃቀም/capitalization፣ በስርአተ ነጥብ እና በስፔሊንግ ደንቦች በቂ ችሎታ ማሳየት።
- የተለመዱ ስርኣተሆሄያት ቅርፀቶች ላሏቸው ቃላት እና ዘወትር ለሚከሰቱ ያልተለመዱ ቃላት የተለመዱ ስርኣተሆሄያት መጠቀም።
- ትምህርት-ያልተሰጠባቸውን ቃላት በድምፅ ኣስተካክሎ መፃፍ፣ በድምፅ ትንተና ክሂሎት/ phonemic awareness እና በስርኣተሆሄያት ልምዶች በመጠቀም።

### አስተያየት

- ርእሱን የሚያስተዋውቁባቸው የኣስተያየት ፅሁፎች መፃፍ ወይም የሚፅፉለትን መፅሃፍ ስም ማስታወቅ።
- ኣንድን ኣስተያየት ማስቀመጥና ለኣስተያየቱ ምክንያት መስጠት።
- የመዝጊያ መልእክት ስጥ/ስጪ።

## ሳይንስ

### ፊዚካል ሳይንስ

- የተለያዩ ነገሮች ሊታዩ የሚችሉ ባህርያትን እና የተሰሩባቸውን ቁሳቁሶች፣ ከምርመራዎች በተገኘ መረጃ በመጠቀም፣ ማወዳደር።
- ነገሮች የሚንቀሳቀሱባቸውን የተለያዩ መንገዶች ማወዳደር።
- በአንድ ነገር እንቅስቃሴ ለውጦች መነሻ ምክንያት የግድ መኖሩን ማብራራት።
- ማግኔቶች በተለያዩ ነገሮች ያላቸውን ተፅእኖ መግለፅ።
- ማግኔቶች በአንዳንድ ነገሮች እንዴት ተፅእኖ እንደሚኖራቸው ለመግለፅ ከአሰሳዎች መረጃዎች መታዘብና መሰብሰብ።

### የህይወት ሳይንስ

- ህይወት ያላቸው ነገሮችን እገዛ ባልተደረገለት ነፃ አይን ለማየት ከመጠን በላይ ጥቃቅን ከሆኑ ክፍሎች ስለ መሰራታቸው ከተካሄዱት ምርመራዎች ማስረጃ መግለፅ።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ባህል

- የተለያየ ባህላዊ የበስተኋላ/ዳራ ያላቸው ሰዎች ስብአዊ ፍላጎቶችን የሚያሟሉባቸው እና ለማህበረሰብ አስተዋጽኦ የሚያደርጉባቸውን መገዶች መታዘብ እና መግለፅ።
- ግለሰቦችና ቡድኖች ከሌሎች ባህሎች እንደሚጋሩ እና እንደሚዋሱ እውቅና መስጠት።
- የሰዎች ቡድኖች እንዴት እርስ-በርሳቸው ግንኙነት እንደሚያደርጉ ማብራራት።

### ታሪክ

- ባለፈውና በአሁኑ ጊዜ መካከል ልዩነቶችን ማገናዘብ።
- የዛሬ እና የረጅም ጊዜ በፊት ህዝብ እና ነገሮች ማወዳደር።

## መረጃዊ/ኢንፎርሜሽናል ማንበብ እና መጻፍ

- በተሰጠ ሥራ ወይም በግል ተፈላጊ መረጃን መለየት።
- ተፈላጊ መረጃን ለማሟላት ጥያቄዎችን መፍጠርና ማሻሻል።
- በልቦለድ እና ልቦለድ-ባልሆነ እና በሃቀኛ ህይወት ውስጥ ግንኙነቶችን መለየት።
- የመረጃ ተፈላጊ ለማሟላት መገልገያዎችን መለየት።
- አሃዞችን/መረጃዎችን በተለያዩ ቅርፀቶች መመዝገብ።
- የተፈለገውን መረጃ/ኢንፎርሜሽን ውጤት/ግኝት/መደምደሚያ ለማጋራት ዝግጅት የተለያየ አይነት ቅርፀት ተጠቀም(ሚ)

## ስነጥበብ

### የሥነጥበብ ፈጠራ እና ከሥነጥበብ ጋር ያለ ግንኙነት

- ስለ ሥነጥበብ ሥራ በርካታ ሃሳቦችን ለማፍለቅ በአንክሮ አጢን/አጢኚ እና መርምር(ሪ)።
- ስለ ቦታ/ሥፍራ ሃሳቦችን ለመግለጽ የሥነጥበብን መሠረታዊ ነገር/ዋና ነገር/ባህርይ እና የንድፍ መርሆችን ተጠቀም/ሚ።
- የተፈለገውን መረጃ/ኢንፎርሜሽን ውጤት/ግኝት/መደምደሚያ ለማጋራት ዝግጅት የተለያየ አይነት ቅርፀት ተጠቀም(ሚ)
- የሥነ ጥበብ መሥሪያዎችን በዘዴ በመጠቀም የእደጥበብ ሥራ እውቀት አዳብር(ሪ)።
- ለቦታ ምላሽ የሥነ ጥበብ ሥራ ይፍጠሩ።
- በተለያዩ ቦታዎች ሰዎች ለምን የእደጥበብ ሥራ እንደሚሠሩ ምክንያቶችን ለይተህ(ሽ) ግለጽ(ጪ)።

## ሙዚቃ

### የሙዚቃ ምላሽ/ዝንባሌ

- የሙዚቃ ድምፆችን አወዳድር/ሪ፦ ፈጣን/ዝግ ያለ፣ ጮክ ያለ/ለስላሳ፣ ረዥም/አጭር፣ ከፍተኛ/ዝቅተኛ።
- ከእንቅስቃሴ ጋር እና ያለእንቅስቃሴ ድምፅ የማይጨምር የማይቀንስ የሙዚቃ ምት መጫወት።
- ተገቢ የአድማጭ ስነምግባሮች ማሳየት።
- የመማርያ ክፍል አፈፃፀሞችን ለመገምገም በመምህር-የተለዩ መስፈርቶችን መግለፅ።

### ሙዚቃ መጫወት፦

- የመማርያ ክፍል የሙዚቃ መሣሪያዎች ላይ የምት እና የድምፅ ለዛ ቅርፀቶች ማስመሰል።
- በመማርያ ክፍል መሳርያዎች ፅኑ ምት ማሳየት/ማቅረብ።
- ያገር ፍቅር ያለበት ዝማሬዎችን በመዘመር ዓላማቸውን መግለጽ።

### የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት

- የቀላል ምትና የድምፅ ቃና ቅርፀቶችን ማንበብ።

### የሙዚቃ ፈጠራ

- ቀላል ምት/የዜማ አወራረድ እና ጣዕመ ዜማዊ ቅጦችን መፍጥር እና በስእላዊ አቀራረብ/iconic representation በመጠቀም መቃኘት።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### ጤና-አራማጅ አካላዊ ብቃትና እንቅስቃሴ።

- የተመረጡ ጡንቻዎችን በስማቸዉና በስፍራቸዉ መለየት።
- ልብና የደምስሮች ለጂምናስቲክ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ መለየትና ማሳየት።
- የሰውነት አካል ለጂምናስቲክ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ መለየት (ልብ፣ ሳምባዎች፣ ቆዳ)።
- የጡንቻዎችን ተግባር መለየት።

### የእንቅስቃሴ ክሂሎቶች እና ፅንሰሃሳቦች

- በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍ፣ ግለሰቦች በተለያዩ ፍጥነቶች እንዴት በመማር ደረጃዎች ውስጥ እንደሚገሰግሱ/እንደሚሻሻሉ እውቅና መስጠት።
- የአንድ ሰው ክሂሎት እድገት ውጤት ከባለፈው ልምድ፣ የተፈጥሮ ችሎታ፣ እና የልምምድ  ውጤቶች የሚመነጭ መሆኑን መገንዘብ።
- እንደ ማጎንበስ፣ መሳብ፣ መንጠራራት፣ መጠምዘዝ፣ መዞር፣ መግፋት፣ መወዛወዝ፣ እና ማንሳትን የመሳሰሉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን መለማመድ።
- ፈጠራዊ የእንቅስቃሴ ክሂሎችን ማዳበር።
- የነጠረን ኳስ ወይም እጅ ከወገብ በታች ሁኖ -የተወረወረን ነገር መያዝ ማሳየት።
- የአካልን ቅርፆች በሚለዋውጡበት ወቅት በድጋፍ መሰረት ላይ ሚዛን መንከባከብ/መጠበቅ።

## የጤና ትምህርት

### የግልና የተጠቃሚ ጤና (PCH)

- የግል ጤንነትን የማሻሻል ወይም የመንከባከብ መንገድ ማብራራት።
- በት/ቤት የሚገኙ የጤና አገልግሎቶችን መለየት።
- በብከላ የተፈጠሩ የጤና ጉዳዮች መለየት።

### ደህንነት እና ምርመራ/ጥያቄ(SI)

- ለአስቸኳይ ሁኔታዎች በሚገባ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ መግለፅ።
- ከቤት ውጭ የጤና ደህንነት የመጠበቅ መንገዶች መለየት።
- በእንስሳዎች አካባቢ ደህንነት የመጠበቅ መንገዶች መለየት።
- መኖርያ ቤት ውስጥ ደህንነት የመጠበቅ መንገዶች መለየት።
- የአንድ አሸማቃቂን ባህርያት መለየት።
- መንገርንና ማሳበቅን መግለጽና መለየት።
- ከባይተዋሮች/ከማያውቋቸው ሰዎች ለመጠበቅ መንገዶችን መለየት።